# መስተንግዶ

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
Tourism Training Institute

ቅጽ 53 ቁጥር 53 ሰኔ 2014 ዓ.ም

## ቱሪዝም ለአብሮነት!!
## *Tourism for Togetherness*



HOSPITALITY

## የቱሪዝም ሰልጣኞች



## የሆቴል ሰልጣኞች



# መስተንግዶ

## ማውጫ

ገጽ


1•.የክቡር ዶ/ር በከር ሻሌ መልዕክት ---------- 1

2• የአቶ ገዛኸኝ አባተ መልዕክት ---------- 2

3• የአቶ አብርሃም ለገሰ መልዕክት ---------- 3

4• የአቶ ዳንኤል በቀለ መልዕክት ---------- 4

5• ቆይታ ከወ/ሮ አስቴር ዳዊት ጋር ---------- 5

6• ቆይታ ከአቶ አብይ ንጉሤ ጋር ---------- 10

8• ሰልጣኞች በደቡብ ኢትዮጵያ ---------- 14

10• ግሪክኛ ሆኖብኛል ---------- 18

11• የ9ኛው የቱሪዝምና እንግዳ ተቀባነት ሳምንት ---------- 21



ዋና አዘጋጅ

አስቴር ተክሌ

አዘጋጅ፡- ዝናቧ ቱኞ


### የዋና አዘጋጅ መልዕክት

"ቱሪዝም ለአብሮነት"

በዚህ መሪ ቃል ለዘጠነኛ ጊዜ የሚከበረው የዘንድሮው የቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት አንጋፋ እና ቀዳሚ ኢንስቲትዩት ነው፡፡ በዘርፉም አንቱ የተባሉ በአገር ውስጥና በውጪ ይህ ሁነትም እነዚህን መሰል ባለሙያዎች አዲሶችን ከቀድሞዎቹ እንዲተዋወቁ ለማገናኘት እድል የሚሰጥ ትልቅ በዓል ነው፡፡

መስተንግዶ መጽሔትም በየዓመቱ የሚከበረውን ይህን ሁነት የተመለከቱ፣ አስተማሪ አዝናኝ ጽሑፎችን ይዛ ቀርባለች፡፡

ሁላችሁንም ከልብ እናመሰግናለን፡፡ መልካም ንባብ፡፡


ስልክ 0115308121

Website: wwwctti.edu.et

Email: info@ctti.edu.et

Facebook፡- (Tourism Training Institute)

Telegram: (Tourism Training Institute)

P. O Box፡ 4350

Addis Ababa

# በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
# ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶች

## ተልዕኮ

 የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን እድገት እና ልማት ለማፋጠን ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የክህሎት ስልጠና እና ትምህርት በመስጠት፤ የምርምር፣ የማማከር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የማህበረሰብ ዓቀፍ ስራዎችን በማከናወን ሃገሪቱ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል::

## ራዕይ

በ2022 የቱሪዝም ዘርፉን በስልጠና ፣ በምርምር እና በቴክኖሎጂ ሽግግር በመደገፍ በአፍሪካ ከሚጠቀሱ አምስት የልህቀት ማዕከላት አንዱ መሆን።

## ዕሴቶች

- እንግዳ ተቀባይነት
- የላቀ አገልግሎት
- ተመራማሪነት
- ልህቀት
- ውጤታማነት

ቱሪዝም ለአብሮነት!» በሚል መሪ ቃል ለሚከበረው 9ኛው የቱሪዝምና የእንግዳ ተቀባይነት ሳምንት እንኳን አደረሳችሁ!



የኢፌዲሪ ሥራ እና ክህሎትሚኒስቴር በዚህ ዓመት በተበታተነ ሁኔታ ሲሰሩ የነበሩ ሥራዎች በአንድ ተሰባስበው፣ተናበው እና ተጣምረው ብክነትን በመቀነስ ለግባቸው በጋራ እንዲሰሩ በሚል እንደ አዲስ ሲዋቀር ለአገሪቱ ገቢ በማስገኘትም ሆነ ለበርካታ ዜጎች ሥራ በመፍጠር በኩል ግንባር ቀደም ሆኖ የተገኘው የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ነው።በማዕከል ደረጃ ከነበረበት ኢንስቲትዩት ተብሎ ትልቅ ድርሻ ተሰጥቶት አንዱ ተጠሪ ተቋማችን ሆኗል።

ስለሆነም በዘርፉ ለሚሰለጥኑ ወጣቶች ጥናትን መሰረት ያደረገ የተሻለ ሥርዓተ ስልጠና በመቅረፅ ለሙያው በሚሰጠው ክብር ልክ መሠረታዊ የስልጠና ለውጦችን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ለዚህም እየሰራን እንገኛለን።

ንድፈ ሃሳባዊ ዕውቀት ከተግባር ልምምድ ጋር ተጣምሮ ፈጣን ውጤት ከሚታይባቸው ዘርፎች አንዱ እና የአገራችንን ገፅታ ለዓለም የምናሳይበት የቱሪዝም ዘርፍ በብቁ ባለሞያዎች እንዲደገፍ ከማድረግ አንፃር የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ላለፉት 53 ዓመታት የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰውኃይል በማቅረብ ለአገራችን የሆቴልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዕድገት የላቀ አስተዋፅኦ እያበረከተ የሚገኝ አንጋፋና ግንባር ቀደም ተቋም እንደመሆኑ በዚህ አጋጣሚ የዕድሜውን ያህል እና አገሪቱ ለዘርፉ በሰጠችው ትኩረት ልክ እንዲራመድ ለማድረግ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከፍተኛ ኃላፊነት ተጥሎበታል።ይህንንም ለማሳካት ተባብረን የተሻለ ለውጥ እንደምናመጣ ሙሉ እምነት አለኝ።

ቱሪዝም ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ እና ተፈጥሮ የቸረችንን ፀጋ እንዲሁም ጠብቀን ያቆየናቸውን ሃብቶች የማሳየት ራስን የማስተዋወቅ ተግባር እንደመሆኑ ለዚሁ ምቹ የሆኑ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ የጎደሉ እንዲስተካከሉ በጋራ መስራትን ግድ ስለሚል ኢንስቲትዩቱ አብሮነትን አጀንዳ በማድረግ ኃላፊነት ወስዶ ለሰራቸው ስራዎች ማመስገን ተገቢ ይሆናል።

ዋና ተልዕኳችን ክህሎት ያለው አምራች ዜጋ ማፍራት እንደ መሆኑ የአንጋፋ ተቋማትን ልምድ ቀምሮ ጉድለታቸውን አስተካክሎ ሥራቸውን ማቀላጠፍ ዜጎችን ለማገልገል ምቹ መደላድል የሚፈጥር በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራበት ነው።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ስር እንደ አዲስ ተዋቅሮ ከማዕከልነት ወደ ኢንስቲትዩት ያደገው የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተሳሰር ስራዎችን በቅንጅት መስራትና ኢንዱስትሪው ላይ ያሉን ሙያተኞችን የማብቃት፤የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማካሄድና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራትን ያከናውናል። ይህም የዋሉ ያደሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል አበረታች ተግባር ነው።

የሰለጠነ በቂ የሰው ኃይል ሲበዛ የዜጎቻችን እንግልት ይቀንሳል፤ተወዳዳሪ መሆን ይቻላል፤ኢንቨስትመንት የመሳብ አቅማችን ይጨምራል፤ አገራዊ ራዕያችንም ይሳካል።ብቃትና ክህሎት ደግሞ ከመደበኛው ትምህርትና ስልጠና ባሻገር ሶፍት ስኪል ብለን በምንገልፃቸው የአስተሳሰብ አድማስን በሚቀይሩ ሃሳቦች ራስን መገንባትን ያካትታል።

የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ኮሌጆችን፣ ኢንስቲትዩቶችን አቅም ለማሳደግ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ስገልፅ እንደቱሪዝም ኢንስቲትዩት ያሉት ደግሞ በአገራዊ ዕቅዱ ከቀዳሚዎቹ ተረታ የተሰለፉ እና ዘርፈ ብዙ

ጥቅም ያላቸው እንደመሆኑ የግሉን ዘርፍ በማስተባበር በየደረጃው ካሉ የፌደራል እና የክልል አመራሮች ጋር በመተባበር ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በተለያዩ ጊዜያት ለሚቀርቡ አገራዊ ጥሪዎች ሰልጣኞችን በማስተባበር ግንባር ቀደም በመሆኑ ሁሌም የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ሲታወስ የሚኖር መሆኑን በመግለፅ የተሳካ የአብሮነት ጊዜ እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ! አመሰግናለሁ

---



**የም/ዋናዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ መልዕክት**

የሀገርና 000የወገንን ፍቅር በመላበስ፣ በእውቀት፣ በስነምግባርና በክህሎት ታንጾ ለመስራት እጁ የተፍታታ፣ ሥራ ለመፍጠርና በሚሰራው ሥራ ጽኑ እምነት ያለው የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራት አስፈላጊ ነው።

ዜጎች የመስራትና ሀብት የማፍራት መብታቸው እንዲከበር መስራት የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ይገባል። ለዚህም ተግባራዊ ሥልጠና፣ የሥራ እድል ማመቻቸትና በአሰሪና ሰራተኞች መካከል የሚኖር ጤናማ ግንኙነት መረጋገጥ የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው። ከዚህ አንፃር የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የስራና ክህሎት ሚኒስቴር አንዱ ተጠሪ ተቋም ሆኖ ተቋቁሟል።

ይኸውም የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሥራ እድል በመፍጠር፣ የኑሮ ውድነትን የሚያረጋጉ ሥራዎችን በመስራት በሀገር የኢኮኖሚ እድገት ጉልህ አስተዋፅኦ በማበርከት የሚታወቅ የሙያ መስክ በመሆኑ ለበለጠ ስኬታማነት ታስቦ የተፈጠረ አደረጃጀት መሆኑን ያመላክታል።

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በዘርፉ የሚሰማሩና የተሰማሩ ዜጎችን በማሰልጠን፣ የዘርፉን አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ባለሀብቶች በማማከር፣ የዘርፉን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ ጥናቶችን በማጥናትና ማህበረሰብን ተጠቃሚ የሚያደርጉ አገልግሎቶችን በመስጠት የዜጎችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ተግባራትን እንዲያከናውን ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

በመሆኑም ከመደበኛ ሥልጠናው ጎን ለጎን ሰልጣኞችን በስፋት የሚያሳትፉ ሁነቶችን በማዘጋጀት የተግባር ሥልጠናውን የሚያጠናክር፣ አዳዲስ ሃሳቦች የሚፈልቁበት፣ የዘርፉ ባለድርሻ አካላት ሥልጠናውን የሚያግዙበትና የሥራ ትስስር የሚፈጥሩበትን ምቹ ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቅብናል።

ስለዚህም በጋራ በመመካከር፣ አዳዲስ ሃሳቦችን በማመንጨት፣ በቡድን መስራትን በመላበስ የሀገርንና የህዝብን ተጠቃሚነት ቅድሚያ የሚሰጥ ትውልድ ማፍራት ከዚህ ዘርፍ የሚጠበቅ በመሆኑ ዘንድሮ "ቱሪዝም ለአብሮነት!" በሚል መሪ ቃል የምናከብረው የሆስፒታሊቲ ሳምንት ሰልጣኞች፣ አሰልጣኞችና ባለድርሻ አካላት ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ በመቀራረብና በመቀናጀት የሚመክሩበት፣ ልምድ የሚቀስሙበትንና በሥራ የሚተሳሰሩበትን ሁኔታ በመፍጠር የሥልጠናውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ያግዘናል ብለን እናምናለን።

ተቋማችን በእንግዳ ተቀባይነት፣ በመልካም ስነምግባር፣ በእውቀትና በክህሎት የታነፁ ለሀገር ግንባታ ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ዜጎችን ለማፍራት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት ወሳኝ ተግባር በመሆኑ በጋራ ለመሥራት በራችን ክፍት መሆኑን እያረጋገጥኩ እንኳን ለ9ኛው የሆስፒታሊቲ ሳምንት አደረሳችሁ እያልኩ ሁነቱ በስኬት እንዲዘጋጅ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ሁሉ ከልብ የመነጨ ምስጋናን አቀርባለሁ።

አመሰግናለሁ!



## የአካዳሚክና ምርምር ዲን አቶ አብርሃም ለገሰ መልዕክት

በተቋማችን ለዘጠነኛ ጊዜ ‹ቱሪዝም ለአብሮነት› በሚል መሪ ቃል ለሚከበረው የቱሪዝም ሳምንት እንኳን አደረሳችሁ፡፡

የቱሪዝም ጥቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ በማደግ ላይ ያሉአገራት ለኢኮኖሚ፣ለማህበራዊ እና ለባህል ያለው ፋይዳ ጉልህ መሆኑን በመገንዘብ ዘርፈ ብዙ ጥረቶች በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አገራችን የዘርፉን እምቅ ሀይል በይበልጥ በመረዳት የቱሪዝም ዘርፍን ከአምስቱ ወሳኝ የልማት የትኩረት መስኮች አንዱ በማድረግ ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡

በኢትዮጵያ ደረጃ የቱሪዝም ልማት በተለይ ለወጣቶች እና ለሴቶች ሰፊ የስራ እድል ከመፍጠሩ ባሻገር፤የውጪ ምንዛሪን በማስገኘት፤ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልን በመደገፍ እና በዘርፎች መካከል ትስስርን በማጠናከር በአገር ሁለንተናዊ ልማት ላይ ከፍተኛ ድርሻ ያለው መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡

በተጨማሪም ዘርፉ ዜጎች በጥቃቅን እና አነስተኛ የስራ ዘርፍ በመደራጀት ስራ ፈጣሪ እንዲሆን ሰፊ እድል የሚሰጥ በመሆኑ አገራችን ኢትዮጵያ ከዘርፉ ብዙ መጠቀም እንደምትችል ሌላኛው አመላካች እንደሆነ ይታመንበታል፡፡

በዚህም ምክንያት መንግስት የማሰልጠኛ ተቋማችን በአዲስ መልክ ለስራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ተጠሪ በማድረግ ከአገሪቱ የልማት አጀንዳዎችጋርየበለጠ በማስተሳሰር

የዘርፉን ውጤታማነት ለማሻሻል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ተቋማችንም አዲሱ አደረጃጀት ከተሰጠው ተልዕኮ አንጻር ምቹ መሆኑን በመረዳት፤ለበለጠውጤታማነትአስፈላጊውንጥረት በማድረግላይይገኛል፡፡

የቱሪዝምን ዘርፍ በሰለጠነ የሰው ሀይል ለመደገፍ ይረዳ ዘንድ ተቋማችንን ቢያንስ በአፍሪካ ደረጃ ተወዳዳሪ የልህቀት ማዕከል ለማድረግ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡የተቋሙን የሰው ሀይል ልማት መገንባት ወሳኙ የልህቀት ማዕከሉ ግንባታ አካል በማድረግ በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባም አቅጣጫ ተመላክቷል፡፡ይህንን ሰፊ እቅድ እውን ለማድረግ በሚንስቴር መስሪያቤታችን በኩል ከፍተኛ ቁርጠኝነት ከመኖሩም ባሻገር፤ከተለያዩ የልማት አጋሮች ጋር በማስተሳሰር ተቋማችን ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኝተደርጓል፡፡ በቅርቡ ብቻ ከዓለም ባንክ (12ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) እና ከጀርመን መንግስት የትብብር ድርጅት (1.5 ሚሊዮንዩሮ) ያገኘነው የገንዘብ ድጋፍ ለወደፊቱ ያለንን ተስፋ አጉልቶ የሚያሳይ ስኬት አድርጎ መውሰድ ይቻላል፡፡

በዚህም ሂደት ውስጥ የተቋማችን ባልደረቦች ተሳትፎ እና ያላሰለሰ ጥረት የሚደነቅ ሲሆን፤ለወደፊትም ይህንን መንፈስ በማጠናከር ለበለጠ ውጤታማነት በትብብር እንደምንሰራ ማሳያ ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በቅርቡ በሸገር የወንዝ ዳር ፕሮጀክት ልማት ላይ የተከናወነው የማማከር አገልግሎት አመርቂ ከመሆኑም ባሻገር፤ ለወደፊትም ግዙፍ የሆኑፕ ሮጀክቶችንም ጭምር በብቃት ለመወጣት የሚያስችል ከፍተኛ አቅም እንዳለን ያሳየን ሲሆን፤የተቋማችን አሰልጣኞች ቁርጠኝነት በተግባር ከታዩባቸው አጋጣሚዎች አንዱእንደሆነይታመናል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ35ኛ ጊዜ የተከበረውን የዓለም ቱሪዝም ቀንን ምክንያት በማድረግ ለሲዳማ ክልል የተዘጋጀው ክልል አቀፍ የጉብኝት ፓኬጅ እና የባህላዊ ምግቦችን በሰነድ የማደራጀት ስራም አንዱ በስኬት ከሚጠቀሱ የአሰልጣኞቻችን የሙያ ውጤት እንደሆነ ተመስክሮለታል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአገር አቀፍ ደረጃ በተሰሩት የሙያ ደረጃ እና የስርዓተ-ስልጠና ሰነድ ዝግጅቶች ላይ ዘርፉን በመምራት እና በማስተባበር የተቋማችን አሰልጣኞች ሙያዊ ተሳትፎ ከፍተኛ እንደነበር ይታወቃል፡፡

በ9ኛው ተቋማዊ የሆስፒታሊቲ እና ቱሪዝም ሳምንት በተለየ መንገድ ሰልጣኞችን መሰረት ያደረገ ኩነት እንዲሆን ከመፈለጉ አንጻር፤ሰልጣኞች ከሌሎች የሚማሩበት፤ የእርስ-በርስ ሙያዊ እና ማህበራዊመስተጋብርየሚፈጥሩበት፤ልዩ ተሰጥኦዋቸውን የሚያሳዩበት፤የስራ እድል የሚፈጥሩበት እንዲሁም የሚዝናኑበት እንደሚሆን ይታመናል፡፡

በመጨረሻም ይህኩነት የተሳካ እንዲሆን የሚችሉትን እና የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ላደረጉ የኮሚቴው ሰብሳቢዎች እና መላው አባላት ያለንን አክብሮት እየገለጽኩኝ፤ለሁሉም የተቋማችን ሰልጣኞች፣አሰልጣኞች፣ የአስተዳደር ሰራተኞች እና የማኔጅመንት አባላት በሙሉ መልካሙን ሁሉ እመኛለሁ፡፡

---------------------------------------------------



## የአስተዳደርና ልማት ዲን አቶ ዳንኤል በቀለ መልዕክት

የአስተዳደርና ልማት ዲን ጽ/ቤት ተቋሙ የሠጠውን ተልዕኮ ለማሣካት ትልቅ ሀላፊነት ያለበት ሲሆን በዋናነት የአካዳሚክና ምርምር ዘርፍን ስራ ለማቀላጠፍና በመንግስት መመሪያ መሠረት አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን በማቅረብ ተቋሙ ለዘርፉ የሚበረክተውን አስተዋፆ የላቀ ለማድረግ አስፈላጊውን ሁሉ ግብዓት የሚያቀርብ ክፍል ነው፡፡

ይህ ክፍል በዋናነት ከግዥና ፋይናንስ፣ ከሠው ሃብት አስተዳደርና ልማት፣ ከንብረትና ጠቅላላ አገልገልት አሠጣጥ፣ ከመረጃ አያያዝና ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም አቅርቦት፣ የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታና ሌሎች በተቋሙ ውስጥ ባለ -ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ ሠራተኛውን ለማንቀሳቀስ የሚሰራ ነው፡፡

እነዚህን ክፍሎች እንደ አስፈላጊነቱ ለማሰራት እንደተግዳሮት የሚታየው ከሌሎች የቴ/ሙ/ማ/ተቋማት አንፃር ብቻ የተቃኘ የግዥ ስርአት መኖሩ በሚፈለገው መጠን ግብአቶችን ለማሟላት የሚያጋጥም ችግር ቢሆንም አጠቃላይ የተቋሙ መዋቅር ከጊዜው እና ከተልኮው ጋር አብሮ የሚያስኬድ እንዲሆን እየተሰራ ነው፡፡

ለተቋሙ ትኩረት ተሰጥቶት ወደ ኢንስቲትዩት ማደጉ እና አዲስ መዋቅር እየተዘጋጀ መሆኑ ወደፊት የላቀ ደረጃ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡ የዘንድሮ ሁነት ለየት የሚያደርገው ሰልጣኞች በፕሮጀክት መልክ እንዲሰሩ መደረጉ ነው፡፡ ይህንን ሁነት ከግብ ለማድረስ የተሳተፉ የተቋሙ መምህራንና ሰራተኞች እንዲሁም ሰልጣኞች ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

----------------------------------------

**“መንግስት ለተቋሙ ትኩረት ስጥቶ ወደ ኢንስቲትዩትነት ማደጉ እና አዲስ መዋቅር መዘጋጀቱ ወደፊት የላቀ ደረጃ ለመድረስ ይረዳናል”**

## 9ኛውየቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት የሁነቱ አዘጋጅ ኮሚቴዎች መልዕክት

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት 53 ዓመታት ያስቆጠረ አንጋፋ ተቋም ሲሆን በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ በተለያዩ ሙያዎች ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አምስት እንዲሁም በዲግሪ መርሃ ግብር ብቁ ባለሙያዎችን በማፍራት ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዓይነተኛ አስተዋፅዖ እያበረከተ የቆየ ተቋም ነው። ኢንስቲትዩቱ በተቋሙ ውስጥ ከኢንዱስትሪው ጋር በመተባበር ከሚሰጠው የንድፈ ሀሳብ፣ የተግባርና የትብብር ስልጠና ባሻገር በየአመቱ ሰልጣኞችን በሙያው የሚፈለገውን ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚያስችል ኢንዱስትሪ ተኮር የመስክ ላይ ስልጠና ያከናውናል። በተጨማሪም ሰልጣኞች በቆይታቸው ያገኙትን የክህሎት ስልጠና ለማላቅ የሚያስችል ዓላማ ያለውና በተለይም በተመረጡ 26 የብቃት አኃዶች ላይ ያተኮረ የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ሳምንት (Tourism and HospitalityWeek) በየዓመቱ ለአንድ ሳምንት የሚቆይ አመታዊ ሁነት (Annual Event) ያከናውናል።

በዚህም ዓመት የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ሳምንት ለየት ባለ መልኩ ለ9ኛ ጊዜ “ቱሪዝም ለአብሮነት (Tourism for Togetherness)” በሚል መሪ ቃል በአገር አቀፍ ደረጃ ቱሪዝም ለማህበራዊ ግንኙነት የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ማስረጽ በሚያስችል መልኩ የሚከናወን ሲሆን፤ ሰልጣኞችን በዋና አዘጋጅነት የማስተባበር ሚናውን እንዲጫወቱ ሰፊ ዕድል የሰጠና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ያካተተ ነው። ዝግጅቱም የእግር ጉዞ፣ ሲምፖዚየም (የጥናታዊ ጽሑፍ ኮንፈረንስ)፣ ኤግዚቢሽን (አውደ ርዕይ)፣ የሥራና አሰሪ ግንኙነት (ጆብ ፌር)፣ የክህሎት ውድድሮች፣ የተሰጥዖ ውድድሮች፣ የስፖርታዊ ውድድሮች፣ የባህላዊ ውዝዋዜዎች፣ የበጎ አድራጎት ስራዎችና ሌሎች ተግባራቶች ያካተተ ሲሆን የተቋማችን ሰልጣኞችም በቂ ክህሎት፣ ሰፊ ልምድና ተሞክሮ ይገበያሉ ተብሎ ይታሰባል።

መልካም የሁነት ሳምንት ለታዳሚዎች እንመኛለን!!ቱሪዝም ለአብሮነት!

Tourism for Togetherness!ዋና አዘጋጆች

## “የኛ ስልጠና ትኩረት ቀጣሪ የሆኑ ሰልጣኞችን ለማፍራት ነው”

### ወ/ሮ አስቴር ዳዊት የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር



*ወ/ሮ አስቴር ዳዊት*

**መስተንግዶ ፦** በቅድሚያ ለቃለመጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከልብ አመሰግናለሁ

ስለራስዎ እና ስለ ቤተሰብዎ ሁኔታ ይግለጹልኝ?

**ወ/ሮ አስቴር፦** ተወልጄ ያደኩት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በወላይታ ዞን ወላይታ ሶዶ ከተማ ነው። ለቤተሰቦቼ ሁለተኛ ልጅ ሲሆን በቤት ውስጥ ታዛዥ ለትምህርትና ሰዎችን ለመርዳት በጣም ቅርብ ሆኜ ነው ያደኩት። አባቴ የቤተክርስትያን ቄስ በመሆናቸው በብዙ ባህሪዬ መንፈሳዊ አገልግሎትን ዝማሬን እና በንባብ የዳበረ የልጅነት እድገት አሳልፌያለሁ። አሁን ባለትዳርና የሶስት ልጆች እናት ነኝ።

**መስተንግዶ ፦** በትምህርት ቆይታዎ ምን ዓይነት ተማሪ ነበሩ?

**ወ/ሮ አስቴር፦** ትምህርቴንም በዚያው በተወለድኩበት ከተማ ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ነው ያጠናቀኩት። ጥሩ ውጤት ከሚያመጡት ውስጥ የሚመደብ ሲሆን በ12ኛ ክፍል ማጠቃለያ ከፍተኛ ነጥብ በማምጣት የመጀመሪያ ዲግሪዬን ከሃዋሳ ዩንቨርሲቲ

ያገኘሁ ሲሆን ሁለተኛ ዲግሪዬን ከኒዘር ላንድ ሀገር ቫንሃል ላረንስቲያን ዩንቨርሲቲ አግኝቻለሁ፡፡

በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ቆይታዬ በንድፈ ሀሳብ የተማርነውን ትምህርት በተግባር እንድንረዳ በደቡብ እና በሰሜኑ የሀገራችን አከባቢዎች ያሉ የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች ላይ ትምህርታዊ ጉብኝት ለማድረግ ችለናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በውጪ ሀገር ቅድሚያ ያደረጉት ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ስለሀገራቸው አጠቃላይ ሁኔታ እና የቱርስት መዳረሻ ቦታዎችን የማስጎብኘት ስራ እና ከዚያም አልፎ ከሀገርቱ ውጪ ያሉ ከፍተኛ የቱርስት መዳረሻ የሆኑ አጎራባች ሀገራትን ጉብኝት እንዲናደርግ እድል ፈጥረዋል፡፡ ዛሬ ላይ እዚህ ተቋም ሲመደብ የተግባር ስልጠና አስፈላጊነትን በሚገባ በመረዳቴ ለዘርፉ ሆነ ለስራው ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ረድቶኛል፡፡

**መስተንግዶ** ፡- ወደ ስራ ዓለም እና ወደ አመራር የመጡበት ሂደትስ?

**ወ/ሮ አስቴር** ፡- የመጀመሪያ ስራ የጀመርኩት በወላይታ ዞን ጤና መመሪያ በኤችአይቪ ዴስክ ላይ አሰልጣኝ ሆኜ ነው የተቀጠርኩት፡፡ ስራዬም ስለኤች አይቪ ኤድስ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ፣ ቫይረሱ በደማቸው ያሉ ህሙማን ከተለያዩ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር በመሆን የመርዳት እና በማህበራት እንዲደራጁ በማድረግ ለሁለት ዓመት ያክል ሰርቼያለሁ፡፡ ወደ ሃላፊነት የመጣሁት በሶዶ ከተማ የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ምክትል ሃላፊ በመሆን ተመደብኩኝ፡፡ ሲቀጥል በደብብ ክልል የሴቶች ጉዳይ ቢሮ የህዝብ ግንኙነት መመሪያ ኃላፊ ሆኜ እንድሰራ እድሉ ሲሰጠኝ ሴቶችን ለማብቃት የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎችን ለሁለት ዓመት ያክል እየሰራሁ ሳለ የውጪ ትምህርት እድል አግኝቼ የሄድኩትም ከዚያ ነው፡፡ ትምህርቴን አጠናቅቄ ሲመለስ በክልሉ ሴቶች ጉዳይ ባለሙያ በመሆን ለአንድ አመት ከሰራሁ ቦኃላ በወላይታ ዞን የሴቶች ጉዳይ በመቀጠል የገጠር ዘርፍ ሃላፊ በመሆን በአመራርነት አገልግያለሁ፡፡

**መስተንግዶ ፡- ወደ አዲስ አበባ የመጡበት ተቋም ከዚያም ከፍ ወዳለ ኃላፊነት የነበረው ሽግግር ምን ይመስላል?**

**ወ/ሮ አስቴር** ፡- ወደ አዲስ አበባ የመጣሁት የአፍሪካ ልህቀት አካዳሚ ውስጥ መንግስት በሰጠኝ ኃላፊነት ተመድቤ እየሰራሁ ሳለ በሴቶች እና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የሴቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሆኜ እንዲሰራም እድል ኣገኘሁ፡፡ በመቀጠል አሁን ወዳለሁበት ተቋም በዋና ዳይሬክተርነት ልመደብ ቺያለሁ፡፡

**መስተንግዶ ፡- ወደ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ሲመጡ ምን ጠብቀው ነበር? ምንስ እሰራለሁ ብለው አሰቡ?**

**ወ/ሮ አስቴር፡-** ወደዚህ ተቋም ከመምጣቴ በፊት የሴቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ እያለሁ የቱሪዝም ዘርፉ ለሴቶች እና ለወጣቶች ከፍተኛ የሥራ እድል የሚፈጥር በመሆኑ ከቱሪዝም ድርጅት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያችሉ የተለያዩ ኘሮፖዛሎችና የመግባቢያ ስምምነቶችን በማዘጋጀት ወደ ተግባር የመግባት ስራ ተጀምሮ ነበር፡፡ወደዚህ ተቋም መምጣቴ ያንን ጅምር የነበረውን ሀሳቤን ልጠቀምበት የሚያስችል ሆኖ ኣግኝቼዋለሁ፡፡ በተመሳሳይ የትምህርት ዝግጅቴም ከቱሪዝም በምግብና መጠጥ ዝግጅት ጋር ተጓዳኝ የሆነ በመሆኑ እንዲሁም በተቋሙ የካበተ ልምድ ያላቸው መምህራን እና ባለሙያዎች የነበሩ በመሆኑ ስራዎችን በጋራ ለመስራት ጥሩ እድል ፈጥሮልኛል፡፡

ወደ ተቋሙ ሲመጣ እሰራለሁ ያልኩት ተቋሙ የተሰጠው ትልቅ ተልዕኮ በመሆኑ ይህንን ተልዕኮ ሁሉም እንዲገነዘብ የማድረግ እና ትልቁ ማነቆ የነበረው የአደረጃጀት እና የመዋቅር በመሆኑ ይህ እንዲፈታ ከተቋሙ ማህበረሰብ እና ባለድርሻ አካላት ጋር ርብርብ በመደረጉ ሊፈታ ችሏል፡፡

**መስተንግዶ ፡- ላለፉት ሶስት ዓመታት ውስጥ ምን መልካም አጋጣሚ ምን ተግዳሮት ነበረብዎ?**

**እንደ መልካም አጋጣሚ**

ወ/ሮ አስቴር፡- መልካም አጋጣሚ ነው የሚለው ተቋሙ 50 ዓመት እድሜ ያለው ኣንጋፋ እና በዘርፉ ብዙ ባለሙያዎችን ያቀፈ እዛው ሳለ በሀገሪቱ ለተከፈቱ ዩኒቨርስቲዎች እርሾ ሆኖ ያገለገለ እና ከፍተኛ ልምድ ያላቸው መምህራንን ያቀፈ ተቋም መሆኑ መልካም አጋጣሚ ነበር፡፡ ሌለው ተቋሙ የ5 ዓመት የ10 ዓመት ግልጽ እቅድ ያዘጋጀበት ሁኔታ ነበር፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአምስት ዓመት እቅድን በሶስት ዓመት ተኩል ላይ ከማናጅመንት ጋር በጋራ ስንገመግም ያልተተገበሩ ውዝፍ ስራዎች በመኖራቸው እቅዱን በመከለስ የአዲስ ተማሪዎችን ቅበላ በሶስት እጥፍ ያደገበት፣ የምልመላ ጣቢያ ከ10 ወደ 39 ከፍ ያለበት፣ የጥናት እና ምርምር ስራ የተጀማመረበት፣ እቅዱ አስከ ፈፃሚ ድረስ ግልጽነት በመፍጠር መታቀድ ማቻሉ እንደተቋም አዲስ የሥራ መንፈስ የተፈጠረበት ጊዜ ነበር። ለትምህርት ጥራት የሚረዱ የሙያ ማሻሻያ፣ የካርኩለም፣የሞጁል ዝግጅቶች በተለይ በክረምት መርሃ ግብር በስፋት ሊከናወን ችሏል።

በየዓመቱ ከስምንት ያላነሱ የምርምር ሥራዎች በመምህራን በኩል መከናወናቸው፣ አገራዊ ፋይዳ ያላቸው የጥናትና ምርምር ሥራዎች መሰራታቸው፣ ከዩኒቨርስቲ እና ከቴክንክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር የትብብር ስራዎች መኖሩ፣ ሀገር አቀፍ የምርምር እና የተለያዩ የውይይት መድረኮች መከናወናቸው እና በአቅራቢያ ላሉ ተቋማት እና ህብረተሰብ ክፍል የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ለመስጠት ጥረት ተደርጓል።

የተግባር ስልጠና ለማከናወን እንዲቻል ገነት ሆቴል በአዋጅ-------- ለተቋሙ መተላለፉ ይታወቃል። ከስልጠናው ጋር ሆቴሉን የማስተሳሰር ሥራ በመሰራቱ ሰልጣኞቻችን የተሸለ ልምድ እንዲቀስሙ እና ጥሩ አቅም ያላቸው እዚያው እንዲቀጠሩ ተደርጓል። ተማሪዎቻችን የተሻለ የትብብር ስልጠና እንዲያገኙ በባለኮከብ ሆቴሎች ውስጥ ለትብብር መመደባቸው ለአብነት ሀያት ሪጀንሲ እና ሸራተን አዲስ ላይ ያሉት ጥሩ ስራዎች ሊጠናከሩና ወደ ሌሎችም ሊሰፉ የሚገቡ ናቸው። በቱሪዝም ትምህርት ክፍል ከቅርብ ዓመት በኋላም በሆቴል የትምህርት ክፍልም ተግባር ተኮር የመስክ ላይ ሥልጠና ላይ በትኩረት እየተሰራ ነው።

የቤተ ሙከራዎች ማደስ ማሻሻልና ማሳደግ ላይ የተሰሩ ሥራዎች ጥሩ ጅምር ናቸው። ከቀድሞ የባህልና ቱሪዝም ሚንስቴር በኩል ከዩ.ኤን.ዲ.ፒ ጋር በመተባበር ለምግብና መጠጥ ት/ት ክፍል የሚያገለግሉ የቁሳቁስ ድጋፎች መኖራቸው፣ የቱሪዝም ትምህርት ክፍል ውስጥ ሙዜም የማደራጀት ሥራ በተቋሙ መሰራቱ፣ የሴቶችና ህፃናት ክፍልን ለህፃናት ማቆያ ሙሉ ቁሳቁስ ድጋፍ መገኘቱ፣ ከኢንባሲዎች እና ከባለድርሻ አካለት የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ መጀመሩ ይበል የሚያሰኝ ነው።

ሌለው ተቋሙ አንጋፋ እንደመሆኑ መጠን ሰፊ ባለድርሻ አካላት ያሉ መሆኑ እና በተለይ ከተቋሙ የተመረቁ ተማሪዎች በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ መኖራቸው ትልቅ እድል ነው። ይህንን እድል ለመጠቀም በየዓመቱ በተማሪዎች የሚከናወነው የቱርዝም እና የሆስፒታሊቲ ሳምንት ላይ እንዲሁም በተለያዩ መድረኮች እየተገኙ የሀሳብ ድጋፍ ቢያደርጉም በቂ ኣይደለም።

በቀጣይ የቀድሞ ተማሪዎች ህብረት እንዲጠናከር በማድረግ በትምህርት መስኩም ተጋባዥ አሰልጣኝ የመሆን፤ ሰልጣኞቻችን ወደ ኢንዱስትሪው ሲሄዱ ጥሩ እውቀት እንዲያገኙ የማድረግ፤ በውጪ ያሉ ለተቋሙ የትምህርት ቁሳቁስ እና ለማህበረሰቡ የስልጠና እና የልምድ ልውውጥ እድል እንዲያገኙ የማድረግ ስራ ላይ በትኩረት መስራት አለብን።

### እንደተግዳሮት /ችግር ሆነው የነበሩ

***ወ/ሮ አስቴር፡-*** ትልቁ ችግር የተቋሙ አደረጃጀት እና መዋቅር ነበር። ቀደም ሲል ኢንስቲትዩት የነበረው ወደ ማዕከል በመውረዱ የሚፈለገውን ያህል ሳይሰራ የቆየ ተቋም ነበር። ተቋሙ የተሰጠው ተልዕኮ በስልጠና፣በጥናት እና ምርምር፣በማማከር፣በቴክኖሎጂ ሽግግር እና ማህበረሰብ አቀፍ ስራዎችን ለመስራት እንዲቻል ተልዕኮ ቢሰጠውም መወቅራዊ አደረጃጃቱ የተሟላ ባለመሆኑ አብዘኛው ሥራ በውስን የሰው ሃይል ወይም በኮሚቴ እንዲሰራ የምናደርግበት ሂደት በራሱ ክፍተቶች ነበሩት። ሌላው ተቋሙ ከላይ ጀምሮ እስከ ታች ድረስ ወጥ የሆነ የሥራ ባህል ተቋማዊ ዕሴት ለመገንባት የሚቀሩና የሚስተዋሉ ክፍተቶች የሚታዩበት እና የአመለካከት ችግር የነበረ ነበር። ከመንግስት የሚመደብልን በጀት በጣም ትንሽ ከመሆኑ በላይ የካፒታል በጀት ባለመኖሩ ዕቅዳችንን ለማሳካት መቸገር እና የበጀት ዝውውር ትልቁ ማነቆ ሆኖ የቆየ ነበር። የተማሪዎች ማደሪያ ባለመኖሩ ተማሪዎቻችን አነስተኛ የኪስ ገንዘብ የሚከፈል በመሆኑ አሁን ካለው የኑሮ ጫና አንጻር ትልቅ ተግዳሮት ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ ለቀጣይ በጀት

ዓመት መንግስት ይህንን ችግር ከግምት በማስገባት የካፒታል ፕሮጀክት መፍቀዱ ችግሩን ይቀርፋል ቢለን እናምናለን፡፡

**መስተንግዶ ፡- ተቋሙ ወደ ኢንስቲትዩት ተመልሶ እንዲያድግ ሁሉም ይጥር ነበር በርስዎ ዘመን መሳካቱ ምን ተሰማዎት?**

***ወ/ሮ አስቴር፡-*** የተቋሙ አደረጃጀት ለብዙ ሥራዎቻችን እንቅፋት ሆኖ በመቆየቱ የተቋሙ ማህረሰብ እና ባላድርሻ አካላትን ጨምሮ ወደ ኢንስቲቱት እንዲያድግ ከፍተኛ ፍላጎት ነበር፡፡ ይህን ለመለወጥ ሁሉም የበኩሉን አድርጓል እናም ብዙ ልፋት ብዙ ምልልስ የዶክመንት ዝግጅት 40 እና 50 ገፅ በየጊዜው እያስተካከሉ መላኩ ኃላፊዎችን ለማሳመን የተሄደበት መንገድ እንባ ቀረሽ የሆኑ ብዙ ክርክሮች አሳልፈን እዚህ ደርሰናል፡፡ ይህ በአንዲህ አንዳለ መንግስት ቱርዝምን አምስቱ የኢኮኖሚ ምሶሶ ውስጥ ያስገባ እና ትኩረት የተሰጠበት በመሆኑ አብዛኛው አቻ ተቋማት ሲታጠፊ ይህ አንደ ሰው ሃይል ልዩ ትኩረት በመሰጠቱ እንደ መንግስትም ልዩ ትኩረት ባማግኘቱ ወደ ኢንስቲቱት ሊያድግ ችሏል፡፡ ለዚህ ስኬት ሁሉም ሥራ ክፍል በሚችለው ሁሉ ያደረገውን ጥረት እያደነቅኩ ለስኬቱ እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ፡፡

**መስተንግዶ ፡- ተቋሙ ተጠሪነቱ ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ወደ ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር መዛወሩ ምን ፋይዳ አለው? ምንስ አዲስ ነገር ይዞልን ይመጣል?**

**ወ/ሮ አስቴር ፡-** ቀድሞ በነበረው አደረጃጀት ባህልና ቱሪዝም ውስጥ መኖሩ ችግር ነበር ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን አሁን ካለው ሚኒስቴር መ/ቤት ጋር ክህሎትን፣ ዕውቀትን እና ተደራሽነትን ስናስብ ከኛ አቻ ከሆኑ ተቋማት ጋር አብረን ካልሰራን እንደ ሀገር ውጤት ማምጣት ይቸግረናል፡፡ ከዚህ ቀደም በነበረን አሰራር ሰርተን አገራዊ ለውጥን እናመጣለን ማለት አይቻልም፡፡ በሥራና ክህሎት ሥር መሆናችን የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት በአንድ ጥላ ስር ሆነው የሚመሩበት ዕድል ነው የተሰጠን፡፡ በሌላ በኩል ለቴክኒክና ሙያ ተቋማት ድጋፍ የሚያደርጉ በርካታ ድርጅቶች አሉ እስካሁን በነበረው ሂደት የዚህ ድጋፍ ተጠቃሚ አልነበርንም አሁን ገና ከጅምሩ ኬ ኤፍ ደብሊው የተባለ የጀርመን ተራድኦ ድርጅት ለተቋሙ ያደረገው የቁሳቁስ ድጋፍ አሁን በጅምር ላይ ያሉ ሥራዎችና ወደፊት በዕቅድ የተያዙትን ስናይ የተሻለ ዕድል ለተቋሙ እንደተፈጠረለት እረዳለሁ፡፡

የእኛ ሰልጣኞች እጃቸው የተፍታታ ወደ ሥራ ዓለም ሲገቡ ሙያውን ያወቁ፣ በራሳቸው መሥራት የሚችሉ፣ ሥራ ፈጣሪዎችን እና ቀጣሪ የሆኑ ሰልጣኞችን ለማፍራት የሚችል ተቋም ሆኖ እንዲቀጥል መስራት ይጠበቅብናል፡፡ እንዲሁም የሌሎችንም ተቋማት አቅም ማጎልበት የሚጠበቅበት በመሆኑ ተቋም የልህቀት ማዕከል መሆንን በተግባር ማስመስከር አለበት፡፡ ሌላው ምንም እንኳን በሥራ እና ክህሎት ሚንስተር ስር ተጠሪ ቢንሆንም የቱሪዘም እንዲሁም የባህልና ስፓርት ሚንስቴር መስሪያ ቤት ጋር በትብብር የሚንሰራቸው ሰፊ ስራዎች አሉ፡፡ ለዚህም እንዲረዳ በሚንስቴር ደረጃ ከተቋማችን ቴክንክ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሊከናወኑ የሚችሉ ስራዎችን በመለየት ወደ ስራ ተገቢቷል፡፡



**መስተንግዶ፡- የአዳዲስ ሰልጣኝ ቅበላን በተመለከተ ምን ታስቧል?**

***ወ/ሮ አስቴር፡-*** አሁን ከሥራና ክህሎት ጋር አብረን መሆናችን አንዱ ጠቀሜታው በአገሪቱ ካሉ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር በአንድ ዘርፍ ስለምንገናኝ በኛ ዘርፍ ያሉ የሥልጠና መስኮችን ሰልጣኞች ባሉበት ቦታ ሆነው የተሻለ ሥልጠና የሚያገኙበትን ሂደት ማመቻቸት ተቋማት ደግሞ ራሳቸውን እንዲያጎለብቱ

የአሰልጣኞች ሥልጠና መስጠት ከኛ ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል እኛ የምንቀበላቸው ሰልጣኞች ቢኖሩ እንኳ አሁን ካለው የኑሮ ጫና አኳያ የኪስ ገንዘብ መስጠት አዋጭ ባለመሆኑ ቢያንስ ማደሪያ እና ምግብ የምናቀርብበት መንገድ እንዲመቻች ከገንዘብ ሚኒስቴርና ከሚኒስቴር መ/ቤታችን ጋር በመነጋገር ካፒታል በጀት ሊመደብ ችሏል፡፡

እነዚህ ሁኔታዎች እስኪሟሉ ድረስ ለሁሉም ኣካላት ግልጽና ተደራሽ ማስታወቂያ ወጥቶ የወጣ ሲሆን በፍላጎት የሚመጡ ሰልጣኞችን ተቀብለን ለማሰልጠን በዝግጅት ላይ ነን፡፡

**መስተንግዶ፡-** በቀጣይ ከእድገቱ ጋር ተያይዞ በርካታ ሥራዎች ይጠበቅብናል፤ ከአመራር፣ ከመምህራን እና ከሰራተኛው ምን ይጠበቃል?

**#ግባችን በሚቀጥሉት 10 ዓመታት በአፍሪካ ቀዳሚ ከሚባሉ 5 የልህቀት ማዕከላት አንዱ መሆን እና በዘርፉ 33 በመቶ ብቻ የሆነውን የሰው ሃይል ወደ 66 በመቶ ማሳደግ ነው፡፡#**

**ወ/ሮ አስቴር** ፡- ግባችን በሚቀጥሉት 10 ዓመታት በአፍሪካ ቀዳሚ ከሚባሉ 5 የልህቀት ማዕከላት አንዱ መሆን እና በዘርፉ 33 በመቶ ብቻ የሆነውን የሰው ሃይል ወደ 66 በመቶ ማሳደግ ነው፡፡ ስለዚህ ካስቀመጥ ነው ግብ ላይ ለመድረስ ቅድሚያ እያንዳንዱ የተቋሙ ማህበረሰብ ራሱን መፈተሽ ይገባዋል፡፡ ተቋማዊ ሪፎርም ቀደም ተብሎ ተዘጋጅቶ በሰራተኛው በባለድርሻ አካላትና በቦርድ ተገምግሞ ግብዓት ተሰጥቶት የተሰራውን ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉም ይመለከተኛል ብሎ ለለውጥ ራሱን ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡ የኛ ዘርፍ ደግሞ በጣም ተለዋዋጭ የሆነ ከዘመኑ የቴክኖሎጂ እድገት ጋር እየዘመነ የሚሄድ በመሆኑ እኛም በዚያ ፍጥነት እንድንሄድ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች አሉ ይህ ደግሞ በመምህራን፣ በአስተዳደር ዘርፍ ያለን ሁላችንንም የሚመለከት ነው፡፡የግዢ ሥርዓቱ ፣ የሰው ሃይል ቅጥሩ አጠቃላይ የመማር ማስተማሩ ስራ ዲጂታላይዝድ ሆኖ መሰራት ይገባል፡፡መሰረተ ልማትን የማሟላት እና ጠንካራ አደረጃጀትን በመቅረጽ ብቃት ያለውን የሰው ሃይል በመፍጠር እና በማብቃት ሁሉም ሰራተኛ እና አመራሩ ለዚህ ሥራ ቁርጠኛ በመሆን ራስን በማብቃት ለጋራ ዓላማ መስራት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

**መስተንግዶ፡-** በመማር ማስተማሩ እና ተቋማዊ አሰራሩን እንደ ተቋም ኃላፊ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**ወ/ሮ አስቴር፡-** የመማር ማስተማር ሂደቱ ጥሩ እንዲሆን መምህራን በኮቪድ ወቅት እና በክረምት ስልጠናው እንዳይቋረጥ በተለያየ መንገድ የራሳቸውን ጊዜ ሰጥተው ስልጠናው

ውጤታማ ያደረጉበት መንገድ በጣም የሚያስመሰግን ነው፡፡ ተቋሙ በምርምርና በማማከር፣ በአጫጭር ስልጠና የተሟላ የሰው ሀይል በሌለበት ሁሉ እየተሰራ ያለው ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል፡፡ የምርምር ሥራዎች በሁሉም ዘርፍ ያሉ መምህራን እና ሰራተኞች አሁንም እንዲሳተፉ ራሳቸውንም እንዲያበቁ ብቻም ሳይን በትንሽ ነገር የመርካት ሁኔታ የሚስተዋል በመሆኑ ይህ አተያይ እና ዳር ተመልካች የመሆን አባዜ መቅረት ይኖርበታል፡፡ ሁሉም የድርሻውን ከተወጣ የጋራ ውጤት የማናመጣበት ምክንያት የለም፡፡

ህገወጥ አሰራሮች ሲኖሩም ፊት ለፊት መታገል ሌብነትን መጸየፍ አለብን፡፡

የስልጠና ክፍሎችን፣ ቤተሙከራዎችን በተገቢው ሁኔታ ማደራጀትና መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ከባለድርሻ አካላት ጋር፣ ከውጪ አገራት ጋር ያሉ ግንኙነቶችን በማጠናከር እና እርስ በእርስ በመተጋገዝ ተቋማችንን ከፍ እንድናደርግ ለሁሉም ጥሪዬን አስተላልፋለሁ አመሰግናሁ፡፡

**መስተንግዶ፡-** ስለሰጡን ጊዜ ከልብ እናመሰግናለን፡፡

---

# ከቱሪዝም ትምህርት ክፍል አስተባባሪ ከአቶ አብይ ንጉሤጋር አጭር ቆይታ

*በዝናቧ ቱቶ*



**መስተንግዶ፡-**ከእኛጋርቃለመጠይቅ ለማድረግ ፍቃደኛ ስለሆንክ እናመሰግናለን፡፡ራስህን አስተዋውቀን አብይማነው? መቼ ወደ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ተቀላቀለ ?

**አቶአብይ፡-**አብይንጉሤ እባላለሁ፡፡ተወለጄ ያደኩት በሲዳማ ክልል አለታ ወንዶ ከተማ ሲሆን በፍላጎት ጎንደር ዩኒቨርስቲን በመቀላቀል በቱሪዝም ማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ በ2002 ዓ.ም አግኝቼ በቀድሞ ስሙ የሆቴልና ቱሪዝምሥራ ማሰልጠኛማዕከል በአሁኑ የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትን በ2003 ዓ.ም በመቀላቀል እየሰራሁ በ2006 በማርኬቲንግ ማኔጅመንት 2ኛዲግሬዬን አግኝቻለሁ፡፡አሁን በተቋሙ የቱሪዝም ትምህርት ክፍል በኃልፊነት እያገለገልኩ ነው፡፡

**መስተንግዶ፡-** በቱሪዝም ትምህርት ክፍል የሚሰጡ የተግባር ስልጠናዎችና የሰልጣኞች ብቃት እንዴት ይታያል?

**አቶአብይ፡-**ብቱሪዝም የስልጠና ዘርፍ በቱርጋይድ፣ በቱርኦፕሬሽን፣በቱሪዝም ማኔጅመንት እንዲሁም በማታና ቅዳሜና እሁድ በዲግሪ መርሃግብር የምናሰለጥን ሲሆን በተግባራዊ ልምምድ የተቋሙን ሰልጣኞች በዘርፉ ተወዳዳሪ በማድረግ ግንባር ቀደም ሰልጣኞችን በማበርከት ላይ እንገኛለን፡፡

-----------------------------------

**መስተንግዶ፡-**ሰልጣኞች ከተመረቁ በኂላ ስራ ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን ያነሳሉ፣ከራስህ ተሞክሮ ምን ትመክራለህ?

**አቶአብይ፡-** በኛ ጊዜ ቱሪዝም ተስፋና ስራ የሌለው እንደሆነ ይቆጠር ነበር፤ነገርግን በኛም ጊዜ ቢሆን የቱሪዝም ሰልጣኞች ዘርፈ ብዙ ስራዎች ላይ መሳተፍ የሚችሉበት አጋጣሚ አለ፡፡በአሁኑ ሰዓት የዲፓርትመንቱ ሰልጣኞች በክበባት በመደራጀት ጠንካራ የሥራ ተሞክሮችን በመቅሰም ላይ ይገኛሉ፡፡መንግስት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረትም ጭምር ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አግባብ መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡

**መስተንግዶ፡-**በቱሪዝም ትምህርት ክፍል በሚቀጥለው ጊዜ በተቋም ደረጃ የተሻለ ስልጠናና የሥራ አካባቢ እንዲኖር ምን ታቅዷል?

**አቶአብይ፡-** የሚቀጥሉትን ጊዜያት የስልጠና ሂደት የተሳካ ለማድረግና ለማዘመን ልዩ ልዩ ቤተሙከራዎችን በመክፈትና ልዩ ኦኤስ እና ካሪኩለም በመቅረጽ ጭምር ለሰልጣኞች ጥራት ያለው እና ጊዜውን የጠበቀ ስልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ በከፍተኛ ጥረት ላይ እንገኛለን፡፡ለወደፊት በሰልጣኞች የስራ ዕድል ፈጠራ ላይ እና ከኢንዱስትሪው ባለሙያዎች ጋር በትብብር ስልጠና ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ እንዲሁም የተለያዩ ሁነቶችን በማዘጋጀት ሂደት ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ ለቱሪዝም እድገት የላቀ አስተዋጽዖ የሚያደርጉበትን ሂደት ማመቻቸት ይሻል፡፡

**መስተንግዶ፡-**ጊዜህን ስለሰጠኸን እናመሰግናለን፡፡

**አቶአብይ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

## ውናኒያ ኮሶዬ ልዩ የተፈጥሮ መስህብ

*በተገን ነጋ የቱርጋይድ ሰልጣኝ!*



ውናኒያ ከጎንደር ከተማ 25 ኪ. ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው የላይ አርማጭሆ ወረዳ በድሮው በችራ አምበዞ፣ ቀበሌ በአሁኑ አምበዞ ፣ችራ፣ አለግ ሙና እና ኮሶዬ ቀበሌዎች ሲያካልል በውስጡ የአምበዞን ሠንሠለታማ ተራራ ጨምሮ ከባህር ጠለል በላይ 3200 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል።

ወደዚህ ውብ የተፈጥሮ ስፍራ ለማቅናት ሁለት አማራጭ መንገዶች ያሉት ሲሆን አንደኛው የወረዳው መዲና ከሆነችው የትክል ድንጋይ ከተማ በመነሳት የሶስት ሰዓታት የእግር ጉዞ ማድረግን ሲጠይቅ ሌላኛውና ተመራጩ ደግሞ ከጎንደር ከተማ በመነሳት ወደ ወገራ መስመር 25 ኪ.ሜትር የመኪና ጉዞ ካደረጉ በኋላ ለ15 ደቂቃ በእግር አቆራርጠው የሚያደርጉት ጉዞ ነው።

ይህ ስፍራ ከጎንደር ወደ ሰሜን ፓርክ በሚጓዙበት ወቅት ነፋሻማ አየርን እየመገበ ቤት ለእንግዳ ብሎ አስተናግዶ የሚሸኝ ልዩ ስጦታ ያለው ቦታ ነው።

ይህ ተፈጥሮ ውበቷን ሙሉ ለሙሉ የለገሰችው ልዩ የመስህብ ሀብት ከአምባው ላይ ሁነው ሲመለከቱት የጋራው ሽንተረር፣ ግራና ቀኝ የሚገኘው ደን እንዲሁም ደኑንና ጋራውን ለሁለት ከፍሎ መሀል ለመሀል የሚያልፈው የአቋቮ ወንዝ ከአራዊቶችና ከአዕዋፋት ድምፅ ጋር ተደማምሮ ቦታውን ሲመለከቱ ህይወትዎ በደስታና ፍሰሐ ይሞላል። በአጠቃላይ ከ60 በላይ ረጃጅም የእፅዋት ዝርያዎች ወደ 20 የሚደርሱ አጥቢያዎች በደኑ ውስጥ በብዛት የሚገኙትን ጭላዳ ዝንጀሮ፤ ጉሬዛ፣ ቀበሮ፣ አውጭ፣ አጉሪት፣ ጥርኝ፣ ጦጣዎቸ፣ አነሮች፣ ገመሬ ዝንጀሮ እና በልባቸው የሚሳቡ (ሪፒታይልስ)፣ የተለያዩ የእባብ ዝርያዎች እና ሌሎች ልዩ ልዩ አእዋፋትና የዱር አራዊቶችን ሲመለከቱ ለተፈጥሮ ያሉት አመለካከት ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ይጨምራል። ህይወትዎን በደን ውስጥ ማኖርን ይመርጣሉ።

"በእውነት መሬት ላይ ነው ያለሁት" የሚል ጥያቄ በውስጥዎ ያጭራሉ።

በአጠቃላይ ይህ በተፈጥሮ ሀብት የታደለና በውስጡ የተለያዩ ተራሮች ሸለቆዎች ይዟል ከነዚህም መካከልም የፈራጅ እና የጎተራ ዱር ፏፏቴዎች የድንጋይ ላይ ድንጋይ ሠንሠለታማ ምድር፣ የሳንጃ ወንዝ ገባር የሆኑት የድልድል እና የላምገዳይ ወንዝ፣ የጩጌ ማሪያም ገዳም፣ የአባ መህነነ_ድንግል የተፈጥሮ ዋሻ ገዳማት፣ የግራምጣ አምባዎች፣የኳሪያ ወንዝ እና የድብሪያን ዝቅተኛው ምድር ጨምሮ ሌሎችም የሰዎች አዕምሮ በአግራሞት የመሳብ ጥበብን የተላበሱ መልካአ ምድር ይዟል።

መጎብኘት ለምትሹ ሁሉ ቦታው ሁሌም ለጉብኝት ክፍት ነው ትዝታዎን ከሚያጭሩበት የእንግዳ ተቀባይነት ጋር!!

## ቆይታ አቶ ሽመልስ ዘገዬጋር



አቶ ሽመልስ ዘገዬ ይባላል፡፡ ተወልዶ ያደገው በሰሜን ሸዋ ደራ ወረዳ ከራባ ቀበሌ ውስጥ ነው፡፡በወቅቱ አካባቢው በትምህርት የታወቀ ባለመሆኑ በትምህርቱ ላይ ብዙ ተጽዕኖ እንዳሳደረበት ይናገራል፡፡ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ በክፍል ውስጥ ውስን ቁጥር ባላቸው ተማሪዎች እንደተማረና አራተኛ ክፍል ሲደርስ ግን በአንድ ክፍል ውስጥ ብቻውን የመማር እድል ገጥሞት ብቻውን ተወዳድሮ በክፍል ውስጥ ወደ ቀጣይ ክፍል መዛወር እንደቻለም የልጅነትጊ ዜውን ያስታውሳል፡፡

አካባቢው በጣም ሞቃት ከመሆኑ የተነሳ ክፍሎቹ ንበጋቢና በተለያዩ ቅጠሎች እየሸፈኑ እንደተማሩ በመግለጽ በወቅቱ ያስተምሩት የነበሩ መምህር ፀጋው፣መምህርት እፀገነትና ኮከቤ የሚባሉትን በህይወቱ ትልቅ ቦታእንደሚሰጥና አሁን ያሉበትን ባያውቅም አመስግኗቸዋል፡፡

ከአምስተኛ ክፍል በኋላ በስንቅ ወደ ሌላ አካባቢ ሄዶ ተማረ ከአንደኛ እስከ አስረኛ ክፍል በደረጃ እያወጣት ምሯል፡፡ ሆኖም ባልታወቀ ምክንያት የ10ኛ ክፍል ውጤት እንዳሰበው ባለማምጣቱ እና በወቅቱ የቴክኒክና ሙያ መማር እንደ ሀፍረት ይቆጠር ስለነበር አማራጭ ሲያፈላልግ የቀድሞ ሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በሬዲዮ ሰልጣኞችን ለመቀበል ማስታወቂያ ሲያስነግር በመስማቱ ለመወዳደር ፍላጎትያድር በታል፡፡

የሆቴል ትምህርት ለመማር ለመወዳደር ልሄድ ነው ብሎ ለቤተሰብ ለመናገር ከባድ እንደነበር ይናገራል፡፡ በኦሮሚያ ልዩ ዞን ለመወዳደር የመጣበትን ሁኔታ ጭምር በመግለጽ“ በዚህ ፈተና ብወድቅ እንኳን መመለስ እንደማልች ልገልጨ ወጣሁ” ይላል፡፡ እንደ አምላክ ፍቃድ ሆኖ በ1999 ዓ.ም በአሁኑ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሰልጣኝ ሆኖ እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ ተምሮ በከፍተኛ ማዕረግ ከክፍሉም ከተቋሙም አንደኛ በመውጣት የዋንጫ ተሸላሚ በመሆን ተመርቋል፡፡ ስልጠናውን ሲከታተል ግን በተለያዩ ሆቴሎች የተለያዩ ስራዎችን በመሥራት ሲመረቅ በሙያው ከሶስት ዓመት የስራ ልምድ ጋር እንደሆነም ገልጿል፡፡

በዚሁ ተቋም በሆቴል ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪውን በማግኘት በትላልቅ ሆቴሎች ማለትም እስከ ኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድረስ ጭምር በሼፍነት እንደሰራና በመቀጠልም ሁለተኛ ዲግሪውን በቢዝነስ ማኔጅመንት በመማር በተቋሙ በመምህርነት እየሰራ ቆይቶ አሁን የሆቴል ትምህርት ክፍል ኃላፊ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል፡፡

በሆቴል ትምህርት ክፍል ኃላፊ እንደመሆንህ የሚሰጡ የተግባር ስልጠናዎችን ና የሰልጣኞች ብቃትን በተመለከተ የትምህርት አሰጣጡም 30% የንድፈ ሀሳብና 70% የተግባር በመሆኑ ሥራ ላይ ሆኖ መማር ለትምህርቱም ጥሩ እንደሆነና በተሞክሮም አቶ ሽመልስ እየሰራ መማሩ እንደጠቀመውና ይበልጡን ሥራ ልምድ ይዞ እንደተመረቀም ይናገራል፡፡

የሰርዓትትምህርትለውጥእሱ በሚማርበት ወቅት በድፕሎማ ይሰጥ የነበረው በመቀየር ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ ወደ ሌቭል በመቀየሩ ሰልጣኞች ከተግባር ይልቅ በንድፈ ሀሳብ ላይ እስከ 95% ስልጠና በመውሰዳቸው ሰልጣኞችን በተግባር ለመመዘን ሁሉ ይቸገሩ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

ይህንን ችግር ለመፍታት በቴክኒክና ሙያ ጥናት በማድረግ የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ ተደርጎ በተቋማችን መምህራንና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን አሻሚ የነበረውን ስያሜ አለም አቀፍ እንዲሆን አድርገዋል፡፡

አሁን ተቋሙ እስከ ሰባት አመት በመታገል ሙያውን የሚመጥን ማለትም 'የምግብ አሰራር ጥበብ' (CULINAR ART) በሚል ቀጣይ ትውልድ በምግብ አሰራሩ ውስጥ ጥበብ እንዳለው አይቶ እንዲወድው የሚያደርግ ነው፡፡ አዲሱን ስልጣኛ በ2014 ዓ.ምበተግባርከዘመኑጋርለማደራጀትወደሥራመገ ባቱንተናግሯል፡፡

ምልመላን በተመለከተ ወደ ቴክኒክና ሙያ ከመግባቱ በፊት ለሙያው ፍላጉት ያለው/ላት፣ቋንቋ፣ በሳይንስ ትምህርት ያለው ውጤት ታይቶ ነበር፤ ወደ ቴክኒክና ሙያ መስፈርት መሰረት ከሆነ በኃላ ከሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች መልማዮችን በመላክ ማምጣት የተሻለ አፈጻጸምና ተደራሽነት ስላለው እኔን የመሰል ሰዎች ተገኝተውበታል ይላል፡፡

ይህ ሙያ ከዕውቀት በተጨማሪም ጥሩ ስነ-ምግባር ይፈልጋል፡፡ ቀና አመለካከት ፣ አብሮ መስራት አቅም ያለው መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ሰው ከቤቱ ወጥቶ ለማረፍ የሚመጣበት በመሆኑ ደስታ የሚፈጥር ስነ-ምግባር ያለውና ታማኝነት መኖር አለበት፡፡ መልካም ስነምግባር በብዙ ጥረትና ያለመሰልቸት ስልጠና በመስጠት የሚገኝ ነው፡፡

የሆቴል እንዱስትሪ ከፍተኛ የሰው ሀይል የሚፈልግ በመሆኑ ሰልጣኞች ወደትምህርት በገቡ በወራት ውስጥ ስራ ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡ በዚህዘርፍበቀን 24 ሰዓት በሳምንት ሰባትቀን በወር 30 ቀን በዓመት 365 ቀናት በሙሉ ሥራላይ መሆን እንደሚቻል በመግለጽ ሥራውን ለማግኘት ደጋግሞ በማንኳኳት ማግኘት ይቻላል፡፡ ሥራው ፍላጎት ተነሳሽነትና ፅናት ይፈልጋል እንጂ በዚህ ዘርፍ ሥራ ማጣት እንደሌለ ይናገራል፡፡

በተቋሙ የሚገኙ መምህራንና ሰራተኞች ኢንዲስቱሪውን ከአለባበስ ጀምሮ መምሰል አለባቸው፡፡ ሆኖም ግን በተቋማችን መምህራንን ከሰራተኛውና ከሰልጣኙ ለመለየት እንቸገራለን ይህ ቀጣይ ቢሻሻል መልካም መሆኑን ይገልጻል፡፡ ሌላው ቢሻሻል የሚለው የሰልጣኝ ቁጥርና የተግባር ስልጠና የሚሰጥበት ክፍልላብ ቢጣጣም የተሻለ ነው፡፡

በተጨማሪም መስተካከል ያለበት ሲቪል ሰርቪስ ለዚህ ተቋም እንዲሁም እንደሀገር ለምግብ አሰራር ጥበብ የሚመደቡ መምህራን መስፈርቱ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ቀጣይ ስጋት ስለሆነ የሚመለከተው አካልም ሆነ የኛ ተቋም ውይይት እንደሚያስፈልገው ጠቁሟል፡፡

ይህ ሙያ በዓለም ላይ ከፍተኛ የሰው ሃይል የሚፈልግና እያደገና እየተወለደ የሚሄድ ሥራ ዘርፍ ነው መዝናናትና መብላት በቴክኖሎጂ የማይተካ በሰዎች ብቻ የሚሰራ በመሆኑ በሳይንሱም እየተጠበበ እስከ ማስተርስና ዶክተሬት ወደፊት የሚሰጥ እንደሚሆንም ይገምታል፡፡

በተቋማችንም እስከ ሳይንቲስቶችን ማፍራት ስለሚጠበቅ ከጊዜው ጋር የሚመጥን አደረጃጀቶችንና ግብዓቶች ካሟላንና ጠንክረን ከሰራን ወደፊት ሰዎች ወደውት የሚገቡበት ፊልድ ይሆናል፡፡

ከሌሎች ዓለም ሀገራት ወደ እኛ የሚመጡ ቴክኖሎጂዎች መልካሙን በመቀበልና ክፉውን በመተው ያሉንን መዳረሻዎች በማልማት በሰው ሀብት ላይም በጥራት በመስራት በሰዎች አመለካከት ለውጥ ላይ ምክሰራን የሚንጠብቀው ሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪ ላይ ልንደርስ እንችላለን በማለት ሀሳቡን ገልጿል፡፡

## የቱሪዝም ትምህርት ክፍል ሰልጣኞች በደቡብ ኢትዮጵያ ያደረጉት ትምህርታዊ ጉብኝት

የቱሪዝም ዲፓርትመንት ሦስተኛ ዓመት ሰልጣኞች በደቡብ ኢትዮጵያ ያደረጉትን ትምህርታዊ ጉብኝት ሁለት ሳምንታትን ቆይቷል፡፡ ትምህርታዊ ጉብኝቱ የተጀመረው በመልካ ቁንጥሬና ጥያ ትክል ድንጋይ ነው፡፡



በዚህ የመጀመሪያ ቀን ጉብኝት የቱሪዝም ትምህርት ክፍል አስተባባሪ አቶ አብይ ንጉሤ እንደገለጹት ሰልጣኞቹ ከዚህ ትምህርታዊ ጉዞ የሚያገኙትን እያንዳንዱን በተዘጋጀው ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ በመሙላት ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው በማሳሰብና በጉብኝቱም ወቅት የቱርጋይድ ሰልጣኞች እንደጎብኚ ብቻ ሳይሆን እንደ አስጎብኝም ሆኖ እንዲሳተፉ እድል ተሰጥቷል፡፡

መልካ ቁንጥሬ በአፍሪካ ሁለተኛው በኢትዮጵያ ብቸኛው ኦፕን ኤር ሙዝየም መሆኑን በመጠቆም ጢያ ትክል ድንጋይ በኢትዮጵያ በዩኔስኮ ከተመዘገቡት ከሚዳሰሱ ቅርሶች አንዱ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡ ቀጣይ መዳረሻችን የሆነው ዶርዜ መንደር ነው፡፡

በጨንቻ ወረዳ በዶርዜ መንደር 12 መንደሮች፣ ባህላዊ ምግቦች፣ ቤት አሰራር እና ባህላዊ ጭፈራቸውም የጎብኚውን ቀልብ ይስባሉ፡፡

ባህላዊ የቤት አሠራራቸው ከሌላው ለየት የሚያደርገው ከ100 እስከ 125 ዓመት ይቆያል፡፡ ቤቱ በየአስር ዓመቱ ከቦታ ወደ ቦታ ከ25 እስከ 30 በሚሆኑ ሰዎች እየተገፋ ፊቀቅ ይደረጋል ይህ ምቤቱ

በምስጥ እንዳይበላና እድሜውም እንዲጨምር የሚረዳው ነው።

ሌላው ከእንሰት የሚዘጋጀው ባህላዊ ምግባቸው እና ከተለያዩ እህል ዘሮች የሚሰራ መጠጥ ተጠቃሽ እንደሆነ በተግባር ለሰልጣኞች ማብራሪያ ተሰጥቷል። በተጨማሪም የዶርዜ ባህላዊ ጭፈራ በባህላዊ አልባሳት አሸብርቆ በእናቶችና በወጣቶች ቀርቧል።

ሰልጣኞቻችን በአርባምንጭ ቆይታቸው ስለከተማዋ በቂመረጃ አግኝተዋል። አርባ ምንጭ ሁለት ከተሞች አሉዋት። አንደኛው ሲቀላ ሲሆን ሌላኛው ሼቻ ነው።



ሲቀላ የንግድ ማዕከል በመሆን ሲታወቅ ሼቻ የመንግስት ተቋማት ይገኙበታል።

በአርባምንጭ ከተማ የሚገኙት ሀይቆች አባያና ጫሞ ይባላሉ። የሀይቆቹ አፈጣጠር በድሮ ዘመን ለሦስት ዓመት ሳይቋረጥ በዘነበው ዝናብ ምክንያት እንደሆነ ይነገራል።

ጫሞ ማለት ትርጉሙ ምሬት ማለት ሲሆን የተባለበት ምክንያት ከጦርነት ሸሽት ሰዎች በህይወት እያሉ እየገቡ የሞቱበት በመሆኑ ስያሜውን አግኝቷል።

ሌላው አርባ ምንጭ ነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ በ1967 ዓምተ መሰረተ ነው፤ 514 ስኩዌር ኪሎሜትር ስፋት ሲኖረው ከ91 በላይ አጥቢ እንስሳት፣ 350 ያህል አእዋፋት፣ከ900 እስከ 1000 እፀዋት የሚገኙበት እንደሆነ የፓርኩ አስጎብኝ አቶ ንጉሴ ደምጦ ተናግረዋል።

በዚህፓርክ 40 ምንጮች፣ የእግዜርድልድይ፣ አዞገበያ፣ ፍልውሃ ልዩ የተፈጥሮ መስህብ ናቸው። የነጭሳር ብሔራዊ ፓርክ የሜዳ አህያ የሚገኝበት እንደሆነም ተገልጿል።

ሌላው በደቡብ ኦሞዞን በና ፀማይ ወረዳ ቆይታ ነው። በናፀማይ ወረዳ ከአዲስ አበባ በ770 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ

ትገኛለች፡፡



በዚህ ከተማ አልዱባ ገበያ በሳምንት አንድ ቀን ማክሰኞ ይገበያያሉ፤ ለግብይት ብቻ ሳይሆን ዘመድ ጥየቃና ወጣቶች ለመተጫጨቢያ እንደሚጠቀሙበት አስጎብኚ አቶ ፍሬው እንድሪስ ተናግሯል፡፡

በገበያው የበና፣ ሐመርና አሪ ብሔሮች እንደሚገበያዩ አስጎብኚው ገልጸዋል፡፡ አንዱን ብሔር ከሌላው የሚለየው በአለባበሳቸው እንደሆነ ተናግሯል፡፡

በደቡብ ኦሞ ዞን ፀማይ ወረዳ አንጋፋው የቀይ አፈር ገበያ ተጎብኝቷል፡፡ በዚህ ዞን ውስጥ ከሚገኙት ወረዳዎች አስደናቂው ወረዳ ዳሰነች ሲሆን በአከባቢው ስምንት ጎሳዎች ሲኖሩት ስድስቱ ተመሳሳይነት እንዳላቸውና ሁለቱ ከኬንያ የመጡ እንደሆኑና አሁን ምግማሾቹ ኬንያ ውስጥ እንደሚኖሩ አስጎቢኚ ማይካ እሳቱ ገልፀዋል፡፡ ልዩ የሚያደርጋቸው ሰው ሲሞት አይለቀስም አባት ቢሞት ወዲያው ልጅ ይቀብራል እንጂ ሌላሰው አይመጣም፡፡ የስራባህ ሪያቸው ወንድ ከብት ከማገድና ከአደን ውጭ ምንም አይሰራም ሴቶች ግን ሁሉንም እንደሚሰሩ ተገልጸዋል፡፡ በምሽት ደግሞ ከቱሪሚ በ32 ኪሎ ሜትር ርቀት የሚትገኘውን በኢቫንጋዲ ጭፈራና በከብት ዝላይ የምትታወቀው ሀመር ተጎብኚታለች፡፡

የደቡብ ኦሞ ዞን ዋና ከተማ የሆነች ጅንካ ከተማ በመድረስ ባህላዊ ሙዚየም የአስራ ስድስትና ከዚያ በላይ ብሔረሰቦች አንድ ቦታ ተደራጅቶ ያለው ተጎብኝቷል፡፡ በጅንካ ከተማ አቅራቢያ የሚገኘው አሪ ብሔር ሲሆን ከሌሎች በሰው ቁጥር እና በተማረ ሰው ብዛት እንደሚበልጡ አስጎብኚው የአሪ ተወላጅ የሆነው ዳንኤል ተናግሯል፡፡ እንደአስጎኒኚው ገለጻ በደቡብ ኦሞ የሚገኙ አብዛኛው ብሔር መነሻው አሪ እንደሆነ ነው፡፡

ቀጣይ መዳረሻችን የነበረው ኮንሶነው፡፡ አስጎብኝያችን አቶ ጉርሾ ጉማሾ እንደገለጸው አከባቢውን ለየት የሚያደርገው የመሬት አቀማመጡና የቤት አሰራር እንደሆነ ነው፡፡ በ18 ዓመት አንድ ጊዜ እስከ ሁለት ሜትር የሚረዝም የጽድ እንጨት ይተከላል፡፡ ‹ጄነሬሽን ፖል› ይባላል፡፡ ይህም ማህበረሰቡ ምን ያህል እድሜ በዛ እንደኖረ የሚያሳውቅ ነው፡፡ አንድ መንደር ዘጠኝ ጎሳ ይኖረዋል፡፡ የአከባቢው ወጣቶች አመሻሽ ላይ በአንድነት የሚጫወቱበትና ካገቡም በኋላ ሚስት ወልዳ ህጻን እስከ ሚያድግ ወደ ቤት እንደይ ገባ ተከልክሎ የሚቆዩበት ወጣቶች ማደሪያ አላቸው፡፡ ይህ የሆነው የወሊድ መቆጣጠሪያ ከመፈጠሩ በፊት ባህላዊ የወሊድ መቆጣጠሪያ መሆኑ ነው፡፡

ማጠቃለያችን ሀዋሳ ከተማ ሲሆን ከተማዋን መጎብኘት እንዲሁም አሞራ ገደል የሚገኙ አእዋፋት እና የጀልባ ላይ ጉዞም ተደርጓል፡፡ በማጠቃለያውም አብያታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ የሚገኙ አእዋፋት መካከል ሰጎኖች ተጎብኝተዋል፡፡ አብያታ ሻላ ፓርክ የሚታወቀው በአዕዋፋት እንደሆነም ተገልጿል፡፡

በመጨረሻም ሰልጣኞችና መምህራን በዝዋይ ሀይቅ የጀልባ ጉዞ አድርገዋል፡፡ በደቡብ ክልል ያሉ መስህቦችን ከሞላ ጎደል ለማስጎብኘት ተሞክሯል፡፡

---------------------------------------------------



## የቴምር የጤና በረከቶች

1. ስብና ኮልስትሮል፡- ከየትኛውም የኮልስትሮል ዓይነቶች የጸዳና በጣም አነስተኛ የስብ መጠን ያለው መሆኑ ክብደት መቀነስ ለሚፈልጉ ተመራጭ ነው፡፡

2. ፕሮቲን፡- ቴምር በፕሮቲንና አስፈላጊ ማዕድናት የበለጸገ መሆኑ ለሰውነት እጅጉን ጠቃሚ ያደርገዋል፡፡

3. ቫይታሚን፡- በቫይታሚን የበለጸገ ነው ቴምር፡ ፡ ከቫይታሚን ዓይነቶች ቢ1፣ ቢ2፣ ቢ3፣ ቢ5፣ ኤ1 እና ሲ ንም አካትቶ ይዟል፡፡

4. ሀይል እና ጉልበት፡- ቴምር ቀላል የማይባል የሀይል ክምችት ስላለውም ንቁና በሀይል የተሞላን እንድንሆን ያስችለናል፡፡

5. ፖታሲየምና ካልሲየም፡- ቴምር የፖታሲየም ክምችቱ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም በልብ በሽታ እንዳንጠቃና አካላችን ውስጥ ያለው የኮልስትሮል መጠን እንዲቀንስ ይረዳል፡፡ ቴምር በአንጻሩ አነስተኛ የሶዲየም መጠን ነው ያለው፡፡ ብዙ ፖታሲየምና ትንሽ ሶዲየም ደግሞ ለጤናማ የነርቭ ስርዓት ወሳኝ ነው፡፡

6. ብረት፡- ቴምር በብረትና በፍሎሪን የበለጸገ መሆኑ ደግሞ ብረቱ የብረት ማዕድን እጥረት ላለባቸው ሰዎች፣ ፍሎሪኑ ደግሞ ጥርስን ከመበስበስ ይከላከላል፡፡

7. ድርቀት፡- ለድርቀትም ቢሆን ውሃ ውስጥ የተነከረ ቴምር መመገብ ፍቱን እንደሆነ ይታወቃል፡፡

8. ሰውነትን ማጽዳት፡- በአልኮል መጠጣት ሳቢያ ሰውነት ውስጥ የሚከማቸውን መርዛማ ኬሚካሎች ከሰውነታችን ውስጥ በማስወገድም ይረዳል፡፡

9. ካንሰር እና የዓይን ችግር፡- የዓይን ህመም ችግርንና የሆድ ነቀርሳ (ካንሰር)ን ለማከምም ብቃት እንዳለው ይታወቃል — ቴምር፡፡

10. የቆዳ ችግር፡- ቴምር የቆዳ ችግሮችን በማስወገድም መልካም ዝና አለው፡፡ ጸጉርን በማፋፋት የጸጉር መሳሳትንም ይከላከላል፡፡

በርከት ያሉ ቪታሚኖችን እና ማዕድናትን በመያዙ ለጤናችን በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይነገርለታል፡፡ ሀይል ሰጪ፣ ፋይበር፣ እንዲሁም ካልሺየም፣ አይረን፣ ፎስፈረስ፣ ሶዲየም፣ ፖታሲየም፣ ማግኒዚየም፣ እና ዚንክ ሚኔራሎች በቴምር ውስጥ የሚገኙ በመሆኑ ቴምርን ለጤና ጠቃሚ ያደርጉታል፡፡

ስለዚህም ቴምርን አዘውትረን መመገብ ለጤናችን ከሚሰጠው ጠቀሜታዎች ውስጥም፦

• የሆድ ድርቀትን ይከላከላል፡- ቴምር በባህሪው የማለስለስ ባህሪ ስላለው ምግብ በአንጀታችን ውስጥ በቀላሉ እንዲዘዋወር በማድረግ የሆድ ድርቀት ለመከላከል ይረዳል፡፡ ለዚህም ይረዳን ዘንድ ቴምሩን በውሃ ውስጥ ዘፍዝፈን በማሳደር ጠዋት ላይ መመገብ ይመከራል፡፡

• ለአጥንት ጤንነት እና ጥንካሬ፡- በቴምር ውስጥ የሚገኙት ማዕድናት ለአጥንታችን ጥንካሬ እና ጤንነት እጅጉን ጠቃሚ እንደሆኑ

ይነገራል። ቴምር እንደ ሴሌኒየም ማንጋኒዝ፣ ኮፐር እና ማግኒዚየም ማእድናትን በውስጡ በመያዙም ለአጥንት ጤናማ እድገት እና ጥንካሬ ጠቃሚ ነው።

• ደም ማነስን ይከላከላል፡- ቴምር በውስጡ በያዘው ከፍተኛ የምግብ ማዕድናት ንጥረ ነገሮች ክምችት የደም ማነስ ችግር ላለባቸው ሰዎች እጅጉን ጠቃሚ ነው።

• አለርጂን ይከላከላል፡- ቴምርን ከሌሎች ለየት የሚያደርገው አለርጂን ለመከላከል የሚረዳውን ሰልፈር ንጥረ ነገር በውስጡ በመያዙ ነው። ስለዚህም ቴምርን አዘውትረን የምንመገብ ሰዎች ለተለያዩ አይነት አለርጂዎች የመጋለጥ እድላችን እጅጉን እንዲቀንስ እንደሚያደርገው ይነገርለታል።

• ለነርቭ ጤንነት፡- በቴምር ውስጥ የሚገኙት ቪታሚኖች የተስተካከለ እና ጤናማ የነርቭ ስርዓት እንዲኖረን ስለሚያደርግም ለጤናችን ጠቃሚ ያደርገዋል።

• ለልብ ጤንነት፡- ቴምር ለልባችን ጤንነት በርካታ ጠቀሜታዎች ስላሉት ተመራጭ ያደርገዋል። ቴምር የልብ ጤንነትን ይጎዳል የሚባለውን የኮሌስቴሮል መጠን የመቀነስ አቅም ስላለው ለድንገተኛ የልብ ህመም እንዳንጋለጥም የረዳናል።

ምንጭ፡- ከፌስ ቡክ

---------------------------------------------

# ግሪክኛ ሆኖብኛል

ግሪክኛ ሆኖብኛል (It's Greek to me) ይላሉ ነጮች "ሊገባኝ አልቻለም" (I don't understand) ለማለት ሲፈልጉ። ስፍር ቁጥር የሌላቸው ቃላት ከወደ ግሪክ ነው የመጡት - እንግሊዝኛ ላይ። ለዚህም ነው የማይገባ/ ግልፅ ያልሆነ ነገር ሲያጋጥማቸው ... ግሪክኛ ሆኖብኛል የሚሉት መሰረታቸው ግሪክ (ጽርእ) ትርክቶች ላይ የሆኑ እንግዳ ቃላት እንደመጠቀም ። ግሪኮች የሚጨበጥ ስልጣኔ ብቻ አልነበረም ለዓለም ያበረከቱት... ተረት የሚመስሉ የአማልክቶቻቸው ትርክትንም እንጂ። እነ ሲግመንድ ፍሩድ (ታላቁ የስነ-ልቡና ልሂቅ) ሳይቀሩ የተለያዩ ስያሜዎችን ከግሪክ Myths ነው የተመሰራቱት። በዚሁ ልንደርደርና በዚህ ዘመን የምንጠቀምባቸው የጥንቲቱ የግሪክ የአማልክት የትርክት አሻራ ያረፈባቸዉን የተወሰኑ ቃላት ላንሳ።

፩. *Achilles Heel* (የአኪለስ ተረከዝ: *የአንድን ሰው ደካማ ጎን ለመግለፅ*): - በግሪኮች ዘንድ አኪለስ ገና ወገቡ ሳይጠና እናቱ (Thetis) *ክክሩ ያድናል* ስትል ወንዝ ወርዳ መላ አካላቱን ስትጠምቀው ተረከዙ ብቻ ነበር ዉሃ ያልነካው። አኪለስም በዚህ ጥብቃ አደገ ተመነደገ... ከግሪክ አገር ግን አንድም የሚገዳደረው ጦር ሰባቂና ዘገር ነቅናቂ አልነበረም። ስንቱን ፍላፃ ያልበገረው፣ ስንቱን የጦርነት አውድማ ላይ ጠላቶቹን ያሽመደመደው አኪለስ ... ለካ ድክመቱ ተረከዙ ነበር። በስተመጨረሻም የትሮዩ ጀብደኛ አኪለስ ... በትሮይ ጦረኞች የተመረዘ ቀስት ድንገት ተረከዙ በመመታቱ ፍጻሜዉን አገኘ።

፪. *The Trojan Horse* (የትሮይ ፈረሶች — *ማታለያ* እንደ ማለት ሲሆን የታሪኩ አመጣጥም እንዲህ ይመዘዛል ... እንደ ሆሜር ድርሰት ትሮዮች ዋነኛ የግሪኮቸ ባላንጣ ነበሩ። አንድዜ የከበቧትን ትሮይ መግቢያ በር ላይ ትልቅ ፈረስ (የእንጨት ፈረስ) በማስቀመጥ ወደ ኋላ አፈገፍጉ። ወደ ኋላ የሚሸሸዉን ጦር ሲያዩ የድል በለስ የቀናቸው የመሰላቸው ትሮዮች ድላቸውን በሚጎንጩበት ሌሊት ...

ጦረኞቹ ግሪኮች ከተደበቁበት የእንጨት ፈረስ እየወጡ ትሮዮችን ጭዳ አደረጓቸው።

፫. *Pandora's Box*፡ነጮች የፓንዶራ ሳጥን ይሉታል … እንደተከደነ ይብሰል፣ እዛ በሩቁ፣ አልያም በአራዳ ቋንቋ የማይሳፈጡት ነገር ሲያጋጥማቸው። የቃሉ አመጣጥ እንደገር ነው … እንደ ግሪኮች ትርክት ፓንዶራ የመጀመሪያዋ የማትሞት እንስት ስትሆን፣ ዝዮስ (የግሪኮች አምላክ) ባልዋ እንጂ እሷ እነዳትከፍትው አስጠንቅቆ አንድ ሳጥን ሰጣት። ነገር ግን ፓንዶራ አትክፍቺ የተባለችውን ለመክፈት ጓጓች። አንድ ቀን ባለዋ (Epimetheus) እስኪተኛ ጠብቃ ሳጥኑን ከፈተችው … ክፋቶች ሁሉ ከሳጥኑ እየወጡ አለምን አጥለቀለቋት።

፬. Oedipus Complex፡ የኦዲፐስ ኮምፕሌክስን ሐሳብ የተዋወቀው በሳይኮአናሊስቱ ሲግመንድ ፍሩድ በ 1899 ነበር… እንደ ፍሩድ አባባል ህጻናት በለቡስ ጥላቸው (unconsciously) ወላጆቻችውን ይከጅላሉ ይላል። ስለዚህም ወንዱ አባቱን፣ ሴቲቱ ደግሞ እናቷን እንደ ጠላት ይቆጥራሉ። ይሄ ጥንውት ኦዲፐስ (ለወንድ)፣ ኤሌክትራ (ለሴት) በሎ ይከፍለዋል… የስን-ልቡና ሊሂቁ ፍሩድ። የነዚህ ቃላት አመጣጥ ከግሪክ Myths የተቀዱ ናቸው። በግሪኮች ትርክት ኦዲፐስ አባቱን ገድሎ፣ እናቱን በማግባቱ በሀገሩና በቤተሰቡ ቸነፈረና ቁጣን ያስከተለ ስለመሆኑ ይነገራል።

፭. Narcissism፡Narcissismን ወደ አማርኛ መመለስ ቢከብድም … *በመደነቅ (ለምሳሌ በገዛ ራስ ምስል) ወይም ራስን በመውደድ ጥልቅ ሐሴትን የመጎናጸፍ አባዜ* … በማለት ልንገልጸው እንችል ይሆናል። ለምሳሌ አንድ ሰው ራሱን አለቅጥ ሲኮፍስ፣ ዓለም በሱ ዙሪያ እንድትሽከረከር ሲሻ ወይም የምትሽከረከር ከመሰለው Narcissist እንለዋለን። እንደየ ደረጃው በህምና ፈውስ የሚያስፈልገውም አይነት Narcissism አለ። የዚህቃል አመጣጥ ከመከረኛዋ ግሪክ ነው። ናርሲስ የሚባል ወንዝ ዳር የሚበቅል ውብ አበባ አለ። ናርሲስ ቀና በሎ ማንንም አይቶ አያውቅም… ቀን ከሌት አንገቱን ከዉሃው እንደተከለ ነው። እሱ ዉሃ ውስጥ ባየው የራሱ መልክ ተማረኮ፣ በፍቅር ወድቋል። እንደ ግሪኮች Myth ከሆነ Echo (የገደል ማሚቶ) በናርሲስ ውበት ተማርኮ የተላከውን ድምጽ ጠፍቶበት የ Narcissusን ድምጽ ሲደጋግም እንደኖረ ይተርካሉ። በአማርኛውም የገደል ማሚቱ ማለት የራሱ ሐሳብ የሌለው የሰውን ሲያስተጋባ የሚኖር እንደማለት አይደል?

በዚህ ዘመን ምዕራባዊያን ከሚያዘወትሯቸው ቃላቶች ለመጥቀስ ያክል፦ The Midas Touch (የነካው ሁሉ ወርቅ የሚሆንለት ወይም ቢዝነስ የሚሳካለት)፣ Leave no stone unturned (ሁሉንም መሞከር)፣ Call a spade a spade (አካፋን አካፋ ማለት፣ ሁሉን በስሙ መጥራት)፣ Spill the beans (አለመደበቅን አልያም ሚስጥርን ማጋለጥ)፣ Touch Wood (መልካም ገድ)፣ Cloud Cuckoo Land (ምናባዊ ሀገር)፣ Cry Wolf (የውሸት/የማስመሰል ለቅሶ፣ የአዞ እምባ)፣ Cassandra (ተስፋና ተስፋቢስነት)፣ Resting on his laurels (ድል መቀዳጀት)፣ Gordian Knot

(ውስብስብ፣ ቋጠሮው የማይፈታ ችግር)፣ To blow hot and cold (ወጥነት የሌለው፣ ለብዎ ቀዝቀዝም ያላለ)፣ Wrong end of the stick (የተሳሳተ አካሄድ፣ የተዛባ አመለካከት) …. ወዘተ ከወደ ግሪክ የሚመዘዝ የየራሳቸው አፈ-ታሪክ አላቸው።

---------------------------------------------------



9ኛው የቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት  አዘጋጅ ኮሚቴዎች (ሰልጣኝ )

# 9ኛው የመስተንግዶ ሳምንት (Hospitality Week)

*(የተከበሩ ሙፈሪያት ካሚል ስለ 9ኛው የመስተንግዶ ሳምንት ከፃፉት)*



“የመስተንግዶ ኢንዱስትሪውን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ተመራጭ ለማድረግ የሚያስችሉ የክህሎት ባለቤት የሆኑ ባለ ብሩህ አእምሮ ወጣቶችን ያየሁበት ነው”

የመስተንግዶ ሳምንት (Hospitality Week) እና የሥራ ትርኢት (Job Fair) 'ቱሪዝም ለአብሮነት' በሚል መሪ ቃል በሚኒስቴር የመስሪያ ቤቱ ተጠሪ ተቋም የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኢንስቲቲዩት አዘጋጅነት ተጀምሯል።

በኢኒስቲቲዩቱ ሰልጣኞች የቀረቡ እጅግ ድንቅ የሆኑ የሆቴልና ቱሪዝምን መስክ ለመለወጥ የሚያስችሉ ስራዎችን የመመልከት ዕድል አግኝቻለሁ። የመስተንግዶ ኢንዱስትሪውን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ተመራጭ ለማድረግ የሚያስችሉ፣ በቋንቋ ክህሎት የተካኑ፣ የቱሪስቶችን ቆይታ ምቹ በማድረግ የቱሪስት ፍሰትን የሚያሳድጉና ቆይታን ለማራዘም የሚጋብዙ፣ የተሻለ ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ ሙያዎችን፣ የክህሎት ባለቤት የሆኑ ባለብሩህ አእምሮ ወጣቶችን ያየሁበት ነው።

በቱሪዝም መስክ የመስተንግዶ ኢንዱስትሪ (hospitality industry) ያልተነካ ዕምቅ አቅም ያለው በመሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዘርፉን ሪፎርም ለማድረግ ከፍተኛ ሀብት መድቦ ስራ ጀምሯል። በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሀይል ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ የማቅረብ ስራችንን አጠናክረን እንቀጥላለን።

የስራ ትስስርን ለመፍጠር ያለመው የሥራ ትርዒት ላይ ያገኘናቸው ዕጩ ምሩቃን በግል ስራ ከተሰማሩ ባለሀብቶች ጋር ከመገናኘታቸውም ባሻገር በራሳቸው ስራ ለመፍጠር ያላቸው ተነሳሽነትና ዝግጁነት የሚደነቅ ነው።

ከኢንስቲቲዩቱ ተመርቀው የራሳቸውን ስራ ፈጥረው ወደ ተግባር የገቡ ወጣቶች ለሌሎች ወጣቶች በርካታ የስራ ዕድል መፍጠር መጀመራቸውን ማየቴ ትልቅ ተስፋ የሰነቅኩበት ነው። በቀጣይ በዚህ መስክ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎችን አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል።

የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችንን ፈለግ በመከተል በኢንስቲቲዩቱ ዙሪያ ለሚኖሩ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖቻችን የማዕድ ማጋራት ፕሮግራምም አካሂደናል። ብለው በማህበራዊ ትስስር ሚዲያቸው አጋርተዋል።

የመክፈቻ ፕሮግራም












www.ethiopia.travel







ሁለተኛ ቀን

ቱሪዝም ለአብሮነት ሲምፖዚየም











ሶስተኛ ቀን የተለያዩ የክህሎት ውድድሮች


Working Station












ስፖርታዊ ውድድሮች







የማጠቃለያ ፕሮግራም













ቱሪዝም ለአብሮነት



ለ9ኛው የቱሪዝምና እንግዳተቀባይነት ሳምንት መክፈቻ ፕሮግራም የተዘጋጀ ኬክ



የሆቴል ሰልጣኞች በሀያት ሪጀንሲ ኢንተርናሽናል ሆቴል




Working

# ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
# Tourism Training Institute

## 9ኛው የቱሪዝምና የእንግዳ ተቀባይነት ሳምንት
## Tourism and Hospitality Week



9ኛው

"ቱሪዝም ለአብሮነት"

"Tourism For Togetherness"

9th

ከግንቦት

21- 26 /2014 ዓ.ም

29- june 3/20 22